# በSEA የሚገኙት የፍተሻ ቦታዎች ለምን አስቸጋሪ ሆኑ?

እርስዎ ወይም ሌላ ሰው ወደ ሲያትል-ታኮማ አለም አቀፍ አየር መንገድ/Seattle-Tacoma International Airport (SEA) ከሚያደርጓቸው የመጨረሻ ጉዞዎች መካከል በአንዱ በደህንነት የፍተሻ ቦታዎች ላይ ረጅም፣ የተቆላለፉ ሰልፎች ሊያጋጥማችሁ ይችላል። ግባችን ሁሉንም ሰው ከ20 ደቂቃዎች ባነሰ ጊዜ ውስጥ እንዲገባ ማስቻል ሆኖ በአጠቃላይ ይህ አማካኝ ነው፤ ሆኖም ስራ በሚበዛባቸው ሰአቶች ይህን መተንበይ የማይቻል በመሆኑ በተለይም ጠዋት ላይ ረጅም ጊዜ መጠበቅ ሊኖርብዎ ይችላል። ይህ ለምን ይፈጠራል? አየር መንገዱ በዚህ ላይ አቅዶበታል?

ከሰራተኞች ምደባ ጀምሮ እስከ ተርሚናላችን አካላዊ መዋቅር ድረስ የሚያጋጥሙ ልዩ የአሰራር ችግሮች አሉ። በርግጥ ለእያንዳንዱ ቀን እቅድ እና የወደፊት የኢንቨስትመንት ስትራቴጂዎች የሚያዘጋጁ የአስተዳደር ቡድኖች አሉን። ለመረዳት እንዲረዳዎ እስኪ አንዳንዶቹን ዝርዝሮች እንመልከት።

### ሰልፎቹ ለምን በሁሉም ቦታዎች ላይ ያጋጥማሉ?

ስራ ከሚበዛበን ሰአቶች መካከል በአንዱ በፍተሻ ቦታዎች በጣም ረጅም ሰልፍ ሊያጋጥምዎ ይችላል። ለአየር መንገድ ረጅም ሰልፍ መሰለፍ የተለመደ ባይሆንም በSEA ከትላልቅ ችግሮቻችን መካከል አንዱ ከተሰራ አስርት አመታት ያለፉት የተርሚናላችን አካላዊ አቀማመጥ ነው። በአጭሩ ተርሚናሉ በተገነባበት ወቅት የዚህን ያክል እንቅስቃሴ ልናስተናግድ እንደምንችል ብናውቅ ኖሮ ዲዛይኑ በዚህ መንገድ አይሰራም ነበር! እነዚህ የቦታ ችግሮች እንዳሉ ሆነው ይህን የምንፈታባቸውን የፈጠራና ውጤታማ ዘዴዎች እየተመለከትን ነው።

በአጠቃላይ SEA እንደ ሌሎች አየር መንገዶች አይነት የመሰለፊያ ቦታ የለውም። ለምሳሌ፡ ከትልቁ የፍተሻ ቦታችን #3 ፊት ለፊት የሚገኘው ቦታ ስፋቱ 7,000 ስኩዌር ጫማ ነው። ይህ ለሌሎች አየር መንገዶች የትንሹ የፍተሻ ቦታ ስፋት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡ ላስ ቬጋስ/Las Vegas ለትልቁ የፍተሻ ኬላቸው ከ20,000 እስከ 30,000 ካሬ ጫማ ቦታ ያላቸው ሲሆን ተመሳሳይ መጠን ያለው አመታዊ የመንገደኛ ቁጥር ያስተናግዳሉ። በአካላዊ አቀማመጥ ደረጃ ከበሩ ቀጥሎ የአየር መንገዱ የቲኬት መቁረጫ ካውንተሮች እና ቀጥሎም የተሽከርካሪ መስመሮች እና ከዚያም የአየር መንገዱ የመኪና ማቆሚያ ጋራጅ ያሉ በመሆኑ ምክንያት ተመሳሳይ ስፋት ያለው ቦታ መክፈት አንችልም።

ስለሆነም በሰው በሚጨናነቁ ጊዜያት በቀና አነጋገር ልክ እንደ ወንዝ አይነት ጠመዝማዛ ረጅም ሰልፎች እንዲኖሩ ፈቅደናል። ለወጪ ተሳፋሪዎች መውጫዎች ወይም የማሳለጫ መድረሻዎች ወይም ለገቢ ተሳፋሪዎች ቋሚ የትኬት መቁረጫ ቦታዎች አለመዘጋታቸውን እናረጋግጣለን። በርግጥ ረጅሙም ሰልፎቹ ከ#3 በስተ ደቡብ እስከ ማሳለጫው (ከB የህዝብ መተላለፊያ የሚወጡ እና በማሳለጫዎች ወደ ሻንጣ መቀበያዎች የሚሄዱ መንገደኞችን በመተው) ከዚያም በዴልታ የቲኬት ካውንተሮች ዙሪያ ተመልሰው እስከ ማስተንፈሻችን ዚግዛግ መስመር ሰርተው ይሄዳሉ። (በርግጥ ይህ የመዝናኛ ፓርክ መስመር ይመስላል!) የፍተሻ ኬላ #2 በተመሳሳይ ማስተንፈሻ ላይ ከሰሜን ጀምሮ ወደ ደቡብ እስከ አለም አቀፍ የቲኬት ካውንተሮች የሚደርስ ረጅም ሰልፍ አለው።

### የከፋ ሁኔታ ቢያጋጥም ምን ይሆናል?

ሰልፎቹ ረጅም በሚሆኑባቸው ሰው በሚበዛባቸው ጊዜያት የከፋ ሁኔታ ቢያጋጥም የፍተሻ ኬላ #3 ብዙ የማስተናገጃ ቦታዎች ስላሉት ብዙዎቹን ሰዎች ወደ የፍተሻ ኬላ #3 የመውሰድ እቅድ አለን። የዚህ ቦታ ሰልፍ ረጅም መስሎ ሊታይ ይችላል ሆኖም ብዙ ጠቅላላ የማጣሪያ መስመሮች ክፍት ከመሆናቸውም በተጨማሪ እጅግ ፈጣን እና ውጤታማ ነው።

ሰልፉ እየጨመረ ከሄደ ሰልፉን እስከ ፍተሻ ኬላ #4 ከD መውጫ ደረጃዎች ወደ ታች እስከ ተንጠልጣይ ድልድዩ እና የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ ድረስ ተመልሶ በሁለት መስመር እንዲታጠፍ እናደርጋለን። እገዛ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች አሳንሰሮች አሉ። ጥያቄዎች ካሉዎ መስመሮቹን የሚያስተናብረውን መንገድ መሪ ይጠይቁ።

በጣም ስራ በሚበዛባቸው ሰዐቶች የመጠበቂያ ጊዜዎች ከ45-60 ደቂቃዎች ሊደርሱ ይችላሉ። ሁሉንም ሰው ስለ ትዕግስቱ እናመሰግናለን። ሰራተኞች በተቻለ መጠን ምን እየተከናወነ እንደሆነ ለማሳወቅ በትጋት ይሰራሉ። ጥያቄዎች ካሉዎ ሰማያዊ/ውሀ ሰማያዊ ወይም ቀይ ሸሚዝ ለባሽ መንገድ መሪዎችን ወይም የደንበኞች አገልግሎት ሰራተኞችን ይጠይቁ።

**ምን ያክል ሰው ሊመጣ እንደሚችል እና ለዚህ መዘጋጀት ስለመቻላችሁ አላውቅም?**

ከውጭ ሲታይ ይህ እጅግ ግልጽ ቀጥተኛ ተግባር ሊመስል ይችላል። TSA በቀን ውስጥ በእያንዳንዱ ሰአት ምን ያክል መንገደኞች ሊመጡ እንደሚችሉ ትንበያዎችን ለማስቀመጥ ከአየር መንገዶች ጋር ይሰራል። እርስዎም ማሰብ እንደሚችሉት የተወሰኑ አሀዞች ሊገመቱ አይችሉም። ትልቁ ትንበያ ለበረራ ደንበኞች የሚደርሱበት ጊዜ ግምት ነው። በረራቸው 10:00 a.m. ሰዐት ነው ቢባል መቼ መምጣት አለባቸው? 8:00 a.m. ሰአት ወይም ቢበዛ እስከ 9:30 a.m. ሰዐት? ወይም በሁለቱ መካከል ባሉት ጊዜያት? የመጠበቂያ ጊዜያት በሚደንቅ ሁኔታ ከአንድ የመጀመሪያ 20 ደቂቃ በቀጣዩ ወደ 30 ደቂቃ ሊለያይ የሚችል በመሆኑ ፈጥኖ መድረስ ሰልፉን ሊቀንስ ይችላል። በተጨማሪም አየር መንገዶች አዲስ ቲኬቶች በሚሸጡበት ወቅት አሀዞቹ ከትንበያዎቹ የተለዩ ሊሆኑ ይችላል።

ሌላኛው ምክንያት ከጠቅላላው 70 በመቶ ያክል የመርከብ ሽርሽር ተሳፋሪዎች ወደ አየር መንገዱ የሚመጡበት ሰው የሚበዛበት የመርከብ ሽርሽር ወቅት ነው። የመርከብ ሽርሽር መስመሮች መንገደኞችን የበረራ ሰዐታቸው ቀን ላይ ቢሆንም እንኳ ጠዋት ሊያወርዱ ይችላሉ። ይህ መተንበይ ባለመቻሉ ላይ ተጨምሮ የመርከብ ሽርሽር መንገደኞች በተለያዩ ደረጃዎች በጣም በጠዋት ቀድመው ወይም ሁሉም አንድ ጊዜ ሊመጡ መቻላቸው ትልቅ መጨናነቅ ይፈጥራል።

**ሁሉንም የፍተሻ ኬላዎች ሰው በሚጨናነቅባቸው ወቅቶች ለምን ክፍት አታደርጓቸውም?**

እንደ ሌሎች አሰሪዎች ሁሉ TSA በPuget Sound ክልል ውስጥ በፍጠነት በሚቀያየረው የኢኮኖመሚ ሁኔታ ሰራተኞችን ለመቅጠርና ይዞ ለማቆየት እየተቸገረ ነው። የTSA አጋሮቻችንን እና በየእለቱ የሚያካሂዱት ጠንካራ ስራቸውን እናደንቃለን (እናንተም በቻላችሁት ጊዜ ‹እንድታመሰግኗቸው› እንጠይቃለን)። ሆኖም አጋሮቻችን ሁሉንም የፍተሻ ኬላዎቻችንን ለመክፈት የሚያስችል በቂ የሰራተና ሀይል ከሌላቸው ይህ የTSA ወኪሎች በአስተማማኝ ሁኔታ መፈተሽ የሚችሏቸው መንገደኞች ብዛት እንዲቀንስ ያደርጋል። የአጋሮቻችን ተግባር ጉዞዎ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማረጋገጥ ነው። በአንድ የሰልፍ መስመር ላይ ጥቂት ኬላዎች ብቻ ክፈት መሆን ማነቆ ሊፈጥር እና ረጅም የመጠበቂያ ጊዜያትን ሊያስከትል ይችላል።

**የሰለጠኑ ውሾችስ? ነገሮችን ፈጣን አያደርጉም?**

TSA በፍተሻ ኬላዎች ላይ ምን ያክል የሰለጠኑ ውሾች እንደሚሰማሩ የተመለከተ ፕሮቶኮሉን ቀይሯል። የአሁኑ ፕሮቶኮል ቀደም ሲል ከነበረበት ይልቅ የዘገየ ከመሆኑም በተጨማሪ በአብዛኞቹ ሁኔታዎች ከየትኛው አጠቃላይ ፍተሻ የፈጠነ አይሆንም።

**ለምን ረጅም መስመር እንድጠብቅ ይነገረኛል? ይህ ትክክል ነው?**

ይህ ብልጠት ሊመስል ይችላል፣ ሆኖም መመሪያው በአብዛኛው ትክክል ነው - ረጅም መስመሮች ፈጣን ሊሆኑ ይችላሉ። ምክንያቱ ተጨማሪ የፍተሻ ኬላዎች ክፍት ስለሚሆኑና የመጠበቂያ ጊዜው ስለሚያጥር ነው። ይህ በአብዛኛው ከብዙ የፍተሻ ኬላዎቻችን ሁለት እጥፍ በሆነው በትልቁ የፍተሻ ኬላ #3 ላይ ይሰራል።

ምን ያክል ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል በተመለከተ የተለመደ የተሳሳተ መረዳት የሚያጋጥመው የሚፈጠረው በማስተንፈሻ #2 እና #3 መካከል በሚፈጠሩት የሚጋጠሙ ረጅም መስመሮቸ የተነሳ ነው። በፍተሻ ኬላ #2 ላይ የሚኖረው መስመር አጭር ቢመስልም እንኳ ብዙ ኬላዎች ስለሚኖሩት ሆኖም በዋናነት ረጅም የመጠበቂያ ጊዜ እናያለን። መንገድ መሪዎች መንገደኞችን ወደ ፍተሻ ኬላ #3 ይመራሉ። አንድ መንገደኛ መስመሩን ተመልክቶ 'አው ይህ መስመር ረጅም ነው፣ ይሄን እያያችሁ እንድሄድ ትፈልጋላችሁ?' ብሎ ሊያስብ ይችላል። እውነታው ግን የመጠበቂያ ጊዜው አጭር መሆኑና መንገድ መሪዎች የትኛው መስመር እንደሚፈጥን መረጃ ያላቸው መሆኑ ነው። መመሪያውን ለመከተል ወይም ላለመከተል ሊመርጡ እና ወደፈለጉት መስመር ሊሄዱ ይችላሉ።

### ተጨማሪ የTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላዎች መጨመር ትችላላችሁ? በጣም ብዙ የTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላዎች አሏችሁ?

በእነዚህ ሁለቱም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎች ይቀርቡልናል። እጅግ ውጤታማ ለመሆን ለTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላዎች ሁለት የፍተሻ ኬላዎች - የፍተሻ ኬላዎች #1 እና #4 ተዘግተዋል። በሰኔ ወር አጋማሽ አየር መንገዱ ለፍተሻ ኬላ #4 አንድ የፍተሻ ኬላ የሚጨምር ከመሆኑም በተጨማሪ በፍተሻ ኬላ #1 መልሶ ማስጀመሪያ በሀምሌ ወር ውስጥ ተጨማሪ ፍተሻ ኬላ ይጨመራል። ይህ ለአምስቱ የፍተሻ ኬላዎች ብዙ የTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላዎች የሚኖሩ መስሎ ቢያሳይም ከተመደቡ ከ25-30 በመቶ የTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላዎች ይልቅ ብዙ ሌሎቸች አጠቃላይ የፍተሻ ኬላዎች እንደሚኖሩ ያስታውሱ። የተፋጠነ ፍተሻ እድል ያግኙም አያግኙም ይህ ወደ ጠቅላላ የፍተሻ ቦታዎች የሚሄዱ መንገደኞችን ብዛት ይቀንሳል። ይህ እውነታ ለCLEAR መስመሮችም ሊሰራ ይችላል። እነዚህ የሚከፈልባቸው አማራጮች ዋጋቸው በተደጋጋሚ የሚወጡ በራሪ ጽሁፎች ዋጋ ያክል ነው።

የአለም አቀፍ አየር መንገድ የቲኬት ካውንተሮችን አልፎ በቲኬት መቁረጫው የደቡብ መጨረሻ ላይ ብዙም የማይታወቅ ሚስጥር ያለ ሲሆን ይህም #1 አሁን ለTSA የቅድመ ፍተሻ ኬላ እና ለCLEAR ደንበኞች በየዕለቱ እስከ 4 p.m. ሰዐት ክፍት መሆኑ ነው።

### ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ረጅም የሰልፍ መስመሮች መቼ መዘጋጀት እችላለሁ?

ትክክለኛ የፍተሻ ኬላ የመጠበቂያ ጊዜያትን ለማግኘት ከስማርት ስልክዎ ላይ የFlySEA መተግበሪያን ያውርዱ። ይዘጋጁ — የመሳፈሪያ ይለፍዎን በቤት ውስጥ ፕሪንት ያድርጉ እና ምን እቃ መያዝ እና አለመያዝ እንደሚችሉ ይወቁ። ቀደም ብለው ይድረሱ — ለሀገር ስጥ በረራዎች ከሁለት ሰዐት በፊት እና ለአለም አቀፍ በረራ ከሶስት ሰዐት በፊት። ዘግይተው በረራዎ ከሚያመልጥዎ ይልቅ በፍጥነት ፍተሻ አለፈው የመጠባበቂያ ጊዜ (ወይም የአዲስ ምግቦችና የቸርቻሮ እቃዎች ናሙናዎች የመምረጫ ጊዜ) ቢኖርዎት ይመረጣል።

### ለፍተሻ ኬላ ሁኔታ የሚረዳ የትኛውንም ነገር ለማድረግ እቅድ አላችሁ?

የSEA Airport ሰራተኞች ለፍተሻ ኬላ ሰልፎች ተጨማሪ መፍትሄዎችን ለማቀድ መስራታቸውን ቀጥለዋል። በዚህ የበጋ ወቅት አራት የሙሉ ሰአት የመንገድ መሪዎችን እና ስምንት መንገድ መሪዎችን ጨምሮ ተጨማሪ ሰራተኞችን ጨምረናል። በተጨማሪም ሰራተኞቹ በሻንጣዎ ምን መያዝ እንደሚፈቀድልዎ እና ምን በቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ውስጥ መጣል እንዳለብዎ በተመለከተ መመሪያ በሚሰጥዎ ወቅት የTSA ሰራተኞችን በተለያዩ ተግባሮች ላይ የሚረዱ የግል ተቋራጭ ቀጥረናል። ለእነዚህ ተግባሮች ተቋራጮችን መጠቀም የTSA ወኪሎችን ተጨማሪ ኬላዎችን እንዲከፍቱ ያስችላቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በፍተሻ ኬላዎች #2, #4, እና #5 ላይ ምን ያክል ሰልፍ ሊኖር እንደሚችል በተሻለ ለመገመት እንዲያስችለን አዲስ አውቶማቲክ የፍተሻ ኬላ ቴክኖሎጂ ስራ ላይ እናውላለን። የኢንፍራሬድ ሲስተም በሪል ታይም መስመሮቹን ፈልጎ በማግኘት መረጃው በተርሚናል የበረራ መረጃ ማሳያዎች እና በFlySEA መተግበሪያ ላይ ይጫናል። የፍተሻ ኬላ #3 በዚህ የበጋ ወቅት መጨረሻ በሲስተሙ ይሸፈናል።

ስለ ወደፊት በመመልከት የወደፊት የደንበኞች አገልግሎት፣ ደህንነት፣ ዘላቂነት እና ውጤታማነት ፍላጎቶችን ለማሟላት ከፍተኛ ኢንቨስትመንቶች ማድረግ ይኖርብናል። የሲያትል ወደብ እና FAA ከ30 ለሚበልጡ የዘላቂ የአየር መንገድ መሪ እቅድ/ Sustainable Airport Master Plan (SAMP) የአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ጥናት እያካሄዱ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ለቀጣይ የተጨማሪ የፍተሻ ኬላዎች መልሶ ስራ ማስጀመሪያ ዲዛይን እና እቅድ ዝግጅት ላይ እየሰራን ነው። ሌሎች የወደፊት ትኩረቶች 19 በሮች እና የኪራይ መኪና አገልግሎት፣ አዲሱን ተርሚናል እና ዋናውን ተርሚናል የሚያገናኙ የሶስት ጣቢያዎች አውቶማቲክ የሰዎች ማጓጓዣዎች ያሉት አዲስ ተርሚናል መስራትን ያጠቃልላሉ። የአጭር ጊዜ ፕሮጀክቶች በ2027 ዓ.ም ይጠናቀቃሉ ወይም ይገነባሉ።

******